# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

ቅጽ 42 ልዩ እትም ቁ. 1 ሰኔ 2007


## አገራችንንና ሕዝባችንን የሚጎዳ ስምምነትን ሁሉ እናወግዛለን!

የኢትዮጵያን የደም ሥር ዓባይን በተመለከተ አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን ለማስጨበጥ እንወዳለን። እነዚህንም በአራት ክፍሎች ለይተን እናቀርባለን።

**1ኛ) *ታሪካዊ ዕውነታዎች፦*** አሁን የያዝነው 21ኛው ክፍለ-ዘመን ዓለም በውኃ እጥረት ምክንያት ከፍተኛ የፀጥታ ስጋት ላይ የወደቀችበት ጊዜ ነው። ለዚህ የውኃ እጥረት በርካታ ዋና ዋና ምክንያቶች ቢኖሩም፣ የሚከተሉትን ሁለት ዓብይ ጉዳዮች ለአብነት ያህል እንጠቅሳለን።

**ሀ) የአየር ንብረት መዛባት፦** የአየር ንብረት መዛባት የዝናብ እጥረትን በማስከተሉ የትልልቅ ወንዞች ውኃ እየቀነሰ መምጣቱን የአየር ንብረት ጠበብቶች ይናገራሉ። እንዲሁም ውኃ ከከርሰ ምድር እያወጡ የሚጠቀሙ አገሮች በዓለም ዙሪያ እየደረሰ ባለው የዝናብ እጥረት ምክንያት የውኃ እጥረትም የሕይወት ከፍተኛ ጥያቄ ሆኗል።

**ለ) የሕዝብ ብዛት መጨመር፦** በዓለማችን የሕዝብ ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ የየአገሮችን የውኃ ፍላጎት በእጅጉ ከፍ እንዲል አድርጎታል። ስለሆነም የተፈጥሮ ውኃ ባለፀጋ የሆኑ አገሮች በከፍተኛ ደረጃ የፀጥታ ችግር እያጋጠማቸው መሆኑን እየተገነዘብን ነው። ኢትዮጵያም በዓባይ ምክንያት ከዚህ ቀደም ተኝተውላት የማያውቁት ጠላቶቿ ሁሉ አሁንም ስለማይተኙላት ለፀጥታዋና ለህልውናዋ አስጊ የሆኑ ሁኔታዎች ሁሉ እየተባባሱ ስለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ሁኔታውን ትኩረት ልንሰጠው ይገባል። የዓባይ ወንዝ ለኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት ይሁን እንጂ በመልካም አስተዳደር እጦትና በብቃት ጉድለት ምክንያቶች ባላት የውኃ ሀብት ላይ መብቷን ተጠቅማ ወንዞቿን ለአገር ዕድገትና ልማት ለማዋል አልቻለችም። አገራችን

ከኤኮኖሚና ከሰው ኃይል ጥንካሬ በተጨማሪ ለሕዝብ መብትና ለሀገር ጥቅም የቆመ መንግሥት ብታገኝ፣ የውኃ ሃብቷን በሕጋዊ መንገድ የመጠቀምና የባለቤትነት መብት ሊነፈጋት ባልተገባ ነበር። በዓባይ ውኃ ምክንያት አገራችን ለብዙ ዘመናት አያሌ ጠላቶችን አፍርታለች። እነዚሁ ጠላቶቻችንም አገራችንን ለማዳከምና ለመበታተን ብዙ ጥረቶችን ሲያደርጉ ኖረዋል፤ አሁንም እያደረጉ ነው። ከእነዚህ አገሮች አንዷ የሆነችው ግብፅ በአገራችን በሰሜኑ፣ በምሥራቁና በምዕራቡ ክፍሎች በተለያዩ ጊዜያት በቀጥታ ጦርነት ከፍታ ለሽንፈት ተዳርጋለች። ይህ በአገራችን ላይ ያደረገችው ቀጥታ ወረራ ቢከሽፍባትም፣ በዓለም መድረክ ላይ የዓባይ ሙሉ ተጠቃሚና ባለቤት ግብፅ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም በማለት ከፍተኛ ድጋፍ እንድታገኝ ያላሰለሰ ጥረት በማድረጓ ብዙ ደጋፊዎችን አፍርታለች።

ግብፅ የዓባይ ባለቤት እኔ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም በማለት በዓለም መድረክ የምትደነፋው "ጌታ ያላት በግ…" በመሆኗ ነው። እንግሊዝና ሌሎች የዓረብ አገሮች በሚያደርጉት የፖለቲካም ሆነ የሥነ-ልቦና ጦርነት ግብፅ ከፍተኛ ድጋፍ ታገኛለች። ስለዚህም ነው ግብፅና ሱዳን ለላይኛው የዓባይ ተፋሰስ አገሮች ምንም እውቅና ሳይሰጡና ምክርም ሳይጠይቁ ብቻቸውን ኢትዮጵያን የሚጎዱ ውሎችን በተለያዩ ጊዜያት የተፈራረሙት። ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር በ1929 ዓ. ም በእንግሊዝ የበላይነት ኢትዮጵያን ለምክር እንኳ ሳያበቁ በተፈራረሙት ስምምነት ግብፅ 48 ቢሊዮን ሜትር ኩቢክ ውኃ እንድታገኝ ያደረገ ሲሆን፣ በግብፅና በእንግሊዝ የጋራ ቅኝ ግዛት ሥር የነበረቸው ሱዳን ደግሞ 4 ቢሊዮን ሜትር ኩቢክ ውኃ እንዲደርሳት የሚያደርግ ነው። ይህም ግብፅ በበጋው ወራት ሙሉ በሙሉ የዓባይን ውኃ እንድትጠቀምበትና እንድትቆጣጠረው የሚያደርግ መብት ያጎናጸፈ ስምምነት ነበር። ከዚህም አልፎ ግብፅ ከላይኛው የዓባይ ተፋሰስ አገሮች ምንም ዓይነት ፈቃድ ሳትጠይቅና ሳይኖራት በዓባይና በገባር ወንዞቹ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ፕሮጀክት ለመሥራት የሚያስችል መብት እንዲኖራት የሚያስከብር ውል ነበር። በዚህ ውል ውስጥ ካልተጠቃለሉትና በማናለብኝነት ካወጡት ሕገ-ደንብ ውስጥ ሌላው ደግሞ፣ ዓባይን ያለእነሱ ፈቃድ ማንም አገር ለእርሻም ሆነ ለኃይል ማመንጭነት መጠቅም አይችልም የሚል ነው። ይህ ማለት እንግዲህ የዓባይ ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያና ሌሎች የዓባይ ተፋሰስ አገሮች በውኃቸው ላይ ያላቸውን ሙሉ መብት በፍጹም የሚነፍግ ነው። እንግሊዝ ይህን ውል ስታፈራርም ኢትዮጵያን

ይቅርና የራሷ ቅኝ ግዛት የነበሩትን ሌሎች የዓባይ ተፋሰስ አገሮችን እንኳን ከምክሩም ሆነ ከውል ስምምነቱ ውስጥ አላካተተችም።

ሌላው ግብፅ እስካሁን ድረስ ሊነካብኝ አይችልም፤ ማንም የመሻር መብት የለውም ብላ የምትመካበት ውል ደግሞ በ1959 ዓ. ም ሱዳን ከእንግሊዞች ነፃ ከወጣች በኋላ ግብፅና ሱዳን የተፈራረሙት ውል ነው። አሁንም እንደገና ኢትዮጵያንም ሆነ ሌሎች የላይኛው ዓባይ ተፋሰስ አገሮችን ሳያማክሩ ግብፅና ሱዳን የተፈራረሙት ይህ ውል የሌሎችን የላይኛው ዓባይ ተፋሳሽ አገሮችን ህልውና ሳይቀር የሻረ ስምምነት ነው። በዚህ ውል መሠረትም ግብፅ 55.5 ቢሊዮን ሜትር ኩቢክ ውኃ እንድታገኝ የተደረገ ሲሆን፣ ሱዳን ደግሞ 18.5 ቢሊዮን ሜትር ኩቢክ ውኃ እንድታገኝ ተደርጓል። ከውሉ ውስጥ አንዱ እንዲያውም ሱዳን የተሰጣትን ተመን እስካላለፈች ድረስ ግድብ መገደብ እንደምትችል ይፈቅዳል። በዚህም መሠረት ሮሲዬርስ የተባለውን ግድብ ጥቁር ዓባይ ላይ ገድባ ለመስኖና ለኤሌክትሪክ ኃይል እየተጠቀመች ነው።

በዚህ ውል ውስጥ ከተጨመሩት ሌሎች ነጥቦች መካከል ኢትዮጵያና ሌሎች የተፋሳሹ አገሮች በዓባይ ላይ የመጠቀም ጥያቄ ካነሱ ግብፅና ሱዳን በጋራ መልስ የሚሰጡ መሆኑንም በውሉ ውስጥ አስፍረዋል። ኢትዮጵያ በየጊዜው የምታቀርበውን የይገባኛል ጥያቄ ግብፅ ከምንም ሳትቆጥር በርካታ ግድቦችን ሠርታ ለመስኖና ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት እየተጠቀመች ነው። በትልቅነታቸው የሚደነቁ መስኖዎችን በመሥራትም ሰፊና በረሃማ የሆነውን ቦታዋን እያለማች ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት ውሎች በቅኝ ግዛት ዘመን የተደርጉ በመሆናቸው ቀደምት የኢትዮጵያ መንግሥታት በበኩላቸው እንዳልተቀበሉት ደጋግመው ማሳወቃቸው በታሪክ ተመዝግቧል። ግብፅ ግን ሁሉም የተፋሰሱ አገሮች ተስማምተው ያፀደቁት በማስመሰል በልበ-ሙሉነት በዓለም መድረክ ሁሉ ዘወትር ስትናገር ይደመጣል። እነዚህ ውሎች ሲፈረሙ አገራችን በምክሩም ሆነ በፊርማው ስለሌለችበት፣ ኢትዮጵያን አይመለከትምና ልትዳኝበት አትችልም ብለን እናምናለን። ሆኖም ግን ግብፅ እስካሁን ድረስ እነዚህ ውሎች ሕያው እንደሆኑ በርግጠኝነት ትናገራለች፤ ምክንያቱም የተፈራረሙት ስምምነት እሷን ብቸኛ የዓባይ ባለቤት የሚያደርጋት ስምምነት ስለሆነ ነው።

ግብፅ በዓባይ ላይ የባለቤትነት ብቻ ሳይሆን የማናለብኝነት ትዕቢትን የተላበሰ ስሜትም ስላላት፣ እስካሁን ድረስ በውኃው ላይ የምተወሰደውን እርምጃ ሁሉ ለላይኛው የዓባይ የተፋሳሽ አገሮች ምንም ዓይነት እውቅና ሰጥታ አታውቅም። ይባስ ብላም ከእራሷ አልፎ ለሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ጥቅም እንዲውል ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ ዕቅድ ነድፋለች። ለምሳሌ የተፋሳሹን አገሮች ሳታማክር የዓባይን ውኃ በስዊዝ ካናል አሻግራ በሲናይ በርሃ ውስጥ ለልማትና ለሕዝብ ሠፈራ ለመጠቀም ከፍተኛ ርብርቦሽ እያደረገች ነው። ይህን የሲናይ በረሃን አቋርጦ የሚሄደውን ውኃም ከልማቱ አልፎ ለሌሎች ዓረብ አገሮች ለመሸጥ ሁኔታውን የሚያመቻች የረዥም ጊዜ ዕቅድ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ይህን ዓባይን ከተፈጥሮ አቅጣጫው ውጭ (natural course) አውጥታ ለጥቅም ለማዋል ማቀዷን አስከትሎ የላይኛው የዓባይ ተፋሳሽ አገሮች ለምን ብለው በጠየቁ ጊዜ ግብፅ ግን የማሳወቅ ግዴታ የለብኝም የሚል በእብሪት የተሞላ መልስ ሰጥታለች። ለዚህም መከራከሪያ ምክንያት የምታደርገው የዓለም የውኃ አጠቃቀም ሕግ የታችኛው የዓባይ ተፋሰስ አገሮች በውኃው ላይ ለሚወስዱትን እርምጃ ሁሉ ለላይኛው የዓባይ ተፋሰስ አገሮች የማሳወቅ ግዴታ የለባቸውም የሚለውን ምክንያት በማድረግ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ግን በዚህ በዓለም የውኃ ተፋሰስ አገሮች የተደረሰውን ውል አስመልክቶ አገራችን ኢትዮጵያ ፈራሚ አገር ስላልሆነች ልትዳኝበት አትችልም እንላለን።

2ኛ) **የሕዳሴ ግድብ አጀማመርና የፅንሰ ሃሳቡ እጸጾች፦** ህወሓት/ኢህአዴግ የሕዳሴ ግድቡን ዕቅድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲገልጽ፣ በአካባቢያችን በሰሜን አፍሪቃና በመካከለኛው ምሥራቅ ከፍተኛ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች በተካሄዱበት ወቅትና አልፎ አልፎም የመንግሥት ግልበጣዎች ይካሄዱ በነበረበት ወቅት ነበር። በዚህ የግርግር ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥም ይህ በዓረብ አገሮች የተቀጣጠለው ግርግር ወደ አገራችን ተዛምቶ አብዮት እንዳይፈነዳ የሕዝቡን የአስተሳሰብ አቅጣጫ ለማስቀየር የተጀመረ ስልት እንደነበር ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል። ምክንያቱም፣ ይህን የመሰለ የልማት ውሳኔ ሲወሰን ህወሓት/ኢህአዴግ በቅድሚያ የአገር ውስጥ ባለሙያዎችን፣ ለምሳሌ የኤኮኖሚ ባለሙያዎችን፣ መሐንዲሶችን፣ የሕግ ባለሙያዎችንና የገንዘብ ምንጭ አፈላላጊ ሰዎችን...ወ.ዘ.ተ አሰባስቦ ማማከር ሲገባው አላማከረም፤ አላደረገውምም። ቢያደርግ ኖሮ የዚህ ምክክር አስፈላጊነትና ከፍተኛ ጠቀሜታው እንደሚከተለው ይሆን ነበር፦

ሀ) **የቅድመ ጥናት አስፈላጊነት፦** አንድን ትልቅ ግድብ ወይንም ትንንሽ ግድቦችን እንደአስፈላጊነታቸው የመገንባት አስፈላጊነትን ለመወሰን ይረዳ ዘንድ ከዚህ በፊት በተለያዩ የውጭ አገር ባለሙያዎች የተጠናውን ጥናት መገምገም ለአገራችን ጠቀሜታ ይኖረው ነበር።

**ለ) በዓባይ ወንዝ ላይ ግድቡ ወይም ግድቦች ሊሰሩ የሚችሉበትን ቦታ መወሰንን በተመለከተ፦** አሁን ግድቡ ያለበት ቦታ በተራራዎች የተከበበ በመሆኑ፣ ለመስኖ ሥራ ጥቅም ለማዋል ውኃውን ወደ መሃል ኢትዮጵያ ስቦ ለማምጣት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ የተመረጠው ቦታ ለሱዳን ወሰን በጣም ቅርብ መሆኑ ለውጭ ጥቃት የተጋለጠ ባልሆነ ነበር።

ሐ) **የዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ጠቀሜታ፦** በግብጽና በሱዳን በኩል የሚመጣውን ተቃውሞ ለመከላከል ቀደም ብሎ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ የዲፕሎማሲ ዘመቻና የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሥራት የግድ አስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም ግብፅ በኢትዮጵያ ላይ ከፍ ያለ ተጽዕኖ ለማሳደር የቻለችው በውጭ ዲፕሎማሲ ብዙ አገሮችን ከጎኗ በማሰለፏ መሆኑ መዘንጋት የለበትምና።

መ) **ግድቡ ለመብራት ብቻ ወይስ ለመስኖ ጭምር የሚለውን ለመወሰን፦** በተፈጥሮ ድርቅና በሰው ሰራሽ ችግር የምትማቅቅ አገር የመብራት ኃይል ሸጣ ከምታገኘው ገቢ ይልቅ ሕዝቡ በመስኖ አምርቶ የሚያመጣው ምርት ለአገሪቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ሊኖረው እንደሚችል ለማጤን ዕድሉ ከፍተኛ ይሆን ነበር።

ሠ) **ግድቡ የሚያስወጣውን ከፍተኛ የገንዘብ ወጭ የሚገኝበትን መንገድ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የገንዘብ አስተዋጽዖ ምንጭን ለመትለም ያስችል ነበር።**

በአጠቃላይ የሕዳሴው ጅማሮ ሲጤን፣ የባለሙያዎችን ዕውቀትና ልምድ በሚጠይቁ ቁልፍ ጥያቄዎች ላይ ውይይት ሳይደረግ እንዲሁ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ትኩረት አቅጣጫ ለማሳት <u>ብቻ</u> ሲባል፣ በተንኮል ተቦክቶና በሸፍጥ ተጋግሮ በግብታዊነት የተተለመ ድርጊት ለመሆኑ አሌ አይባልም። ለዚህም የሕዳሴው ፅንሰ ሃሳብ ቀደም ሲል ከመንግሥት የአምስት ዓመት የሥራ ዕቅድ ውስጥ አለመኖሩ በቂ መረጃ ነው። ስለሆነም፣ ይኸውና ዛሬ የሕዳሴው ግድብ በአያሌ ችግሮች ተተብትቦና እጅ ከወርች ታስሮ ይገኛል።

**3ኛ) የኢትዮጵያ ልማት ቀዳሚነት፦** ለዓባይ የውኃ መጠን ድርሻ የሚያበረክቱ ዘጠኝ የሚደርሱ የዓባይ ተፋሳሽ አገሮች ቢኖሩም፣ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን የውኃ መጠን የምታበረክተው ግን ኢትዮጵያ ናት። የላይኛውና የታችኛው ተፋሳሽ አገሮች በእኩልነት የሚጠቀሙበት ሥርዓት እንዲኖር አንዳንድ ዓለም አቀፍ ሕጎች ቢደነግጉም፣ ኢትዮጵያ ድህነትና ኋላ-ቀርነት አንቆ የያዛት በመሆኗ ጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባ ነበር ብለን እናምናለን። ኢትዮጵያ በዘመናዊ ታሪኳ ማንም የተፋሳሹ አገሮች ያልደረሰባቸው የድርቅ ጥቃት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝቧን ጨርሶባታል። ይህም ብሔራዊ ውርደት የዓለም መዘባበቻና ተመጽዋች አገር እንድትሆን አድርጓታል። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየው የኢትዮጵያና የግብፅ ከፊል ልማት ሲነፃፀር ልዩነቱ የሰማይና የምድር ያህል መሆኑን ማየት ይቻላል።

| | የሕዝብ ብዛት (2012) | የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ | የዘመናዊ ውኃ የማያገኘው | በእንጨትና በከሰል ተጠቃሚ |
|---|---|---|---|---|
| ግብፅ | 80.7 ሚሊዮን | 76.7% | 0.7% | 0.3% |
| ኢትዮጵያ | 91.7 ሚሊዮን | 0.4% | 48.5% | 76.4% |

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ እንደ አብዛኞቹ የዓባይ ተፋሳሽ አገሮች ኢትዮጵያም አስተማማኝ ዝናብ አታገኝም። እንዲያውም ለድርቁ ዋናው ምክንያት የዝናብ ማነስ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ዝናብ ሲገኝ ደግሞ ከፍተኛ ጎርፍ እየፈጠረ በንብረትና በሰው ሕይወት ላይ ብዙ ጥፋት ያደርሳል። በተጨማሪም፣ ኢትዮጵያ ከተፋሳሽ አገሮች ሁሉ በሕዝብ ብዛት ቀዳማዊውን ቦታ ይዛ ትገኛለች። እነዚህ ተጠቃሽ ምክንያቶች ተጨማምረው፣ በዓባይ ተፋሳሽ አገሮች ላይ ለሚደረጉ የልማት ዕቅዶች ትልቁን የውኃ ድርሻ የምታበረክተው ኢትዮጵያ በመሆኗ ከፍተኛውን የውኃ ድርሻ ልታገኝ ይገባታል።

**4ኛ) በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ )በኩል አጥጋቢ ስምምነት የምንለው፦**

*ሀ) የኢትዮጵያን ድህነት ሊቀርፉ ከሚችሉ ተግባሮች አንዱ የመስኖ እርሻ ልማት በመሆኑ የግድቡ ውኃ የኃይል ማመንጫ ብቻ ሳይሆን፣ በዋነኛነት ለመስኖ እርሻም መዋል ሲችል ነው። በተለይም የግድቡ ውኃ የሚውለው ለኃይል ማመንጫነት ብቻ ከሆነ፣ የኤሌክትሪክ መብራት በሌሎች "ንፁህ" በሚባሉ አማራጮች ለምሳሌ ያህልም የነፋስና የፀሐይ ኃይል አመንጭነት መጠቀም ወደፊት ስለሚስፋፋ የኤሌክትሪክን ገበያ በአንፃራዊ ሊያሳንሱት ይችላሉ ብለን እናምናለን።*

ለ) ግድቡ እስኪሞላ ድረስ ለሱዳንና ለግብፅ የሚሰጠው የውኃ መጠን የኢትዮጵያን ጥቅም ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት እንላለን።

ሐ) ግድቡ በደለል እንዳይሞላና የደለል ጠረጋው ደግሞ ዋናውን ትኩረት እንዳይወስድ የዓባይ የታችኛው ተፋሰስ አገሮች ከወጭው ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።

መ) የዓለም አቀፍ የገንዝብ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ልዩ ጥቅምና ከተፋሳሽ አገሮች ጋር የምታደርገውን ትብብር ግምት ውስጥ በማስገባት ግድቡ እንዲጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ወጭ በብድርና በዕርዳታ ሊሰጡ ሲችሉ ነው ብለን እናምናለን።

ሠ) አስዋንና ሕዳሴ ግድቦች በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ ሁለቱ ትልልቅ ግድቦች ስለሚሆኑ፣ በተራዘመ ድርቅ ወቅትና በከፍተኛ ዝናብ ወቅት አጠቃቀማቸውን በስምምነት ማስተባበር አስፈላጊ ነው።

እስካሁን ለግድቡ ጥናት ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ለተቋራጮች የተከፈለ ቢሆንም፣ አንኳር የሆኑ ጥያቄዎች ሳይመለሱ በእንጥልጥል ላይ ይገኛሉ። ለምሳሌ የኮርቻ ግድቡ መጠናቀቅና እንደታሰበው ውኃውን ባያስቀር የሚያደርሰው ጉዳትና ለሽያጭ የሚቀርበው የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመር የመዘርጋት ወጭ መጋራትን አስመልክቶ ዕቅድ አለመኖር ይገኙበታል።

በመጨረሻም፣ ይህ በኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር አማካኝነት የተፈረመው የመግባቢያ ውል ኢትዮጵያን የባሮን፣ የአትባራንና የአቆቦን ወንዞች ለግድብም ሆነ ለእርሻ ጥቅም እንዳታውል ማሰሪያ የሚያደርግ ውል ነው። ምክንያቱም ውኃን ሌሎችንም ሳይጎዳ በአግባቡ መጠቅም አለባቸው ማለት የጥቁር ዓባይ ገባር ወንዞች ሁሉ የሚነሱት ከኢትዮጵያ እንጂ ከሱዳን ባለመሆኑ፣ ውሉ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጎዳው ኢትዮጵያን ነው።

ስለሆነም፣ በኢ.ሕ.አ.ፓ (ዴሞክራሲያዊ) በኩል ከላይ የተጠቀሱት የመፍትሄ ሃሳቦች አሁን በሥልጣን ላይ ባለው በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ አማካይነት ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ብሎ ስለማያምን፣ ኢትዮጵያውያን የሕግና የውኃ አጠቃቀም ባለሙያዎች በአንድነት ተጠናክረው መሥራትና የመፍትሄ ሃሳብ መፈለግ አለባቸው ብሎ ያምናል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ዓባይን የመጠቀም መብታችን በሕዝባችን ኃይል ይከበራል!